# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

የግንቦት 7 ድምጽ፤ ቁጥር 314 ግንቦት 8 2006 ገጽ


ግንቦት 7 የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ በማናቸውም የኢትዮጵያ ግዛት የሚደርስን የሰብዓዊ መብት ጥሰትን በፍጹም ቁርጠኝነት በጋራ እንታገል፤ በስሜት ከተሞሉና ለእርስ በርስ ግጭቶች ከሚዳርጉ ነገሮች እንቆጠብ፤ አርቆ አስተዋይነትና ታጋሽነት በተላበሰ መንገድ የጋራ ጠላቶቻችን በሆኑትን በህወሓት እና አጫፋሪዎቹ ኦህዴድ፣ ብአዴን እና ደህዴድ ላይ በጋራ እንነሳ ሲል ለመላው ኢትዮጵያ ሕዝብ ጥሪ ያደርጋል።

ከግንቦት 7 ዕርሰ-አንቀጽ የተወሰደ (ገጽ-2)

## ዝክር ለግንቦት 7 1997 እና ለግንቦት 7 ቀን 2000 ዓ.ም.

(የግንቦት 7 መግለጫ)

ዘንድሮ፣ የታሪካዊው ግንቦት 7 ቀን 1997 አገር ዓቀፍ ምርጫ ዘጠነኛ ዓመት እና ንቅናቄዓችን የተመሠረተበት ስድስተኛ ዓመት የምንዘክረው ከመቸውም በላይ አገራችን አሳሳቢ ሁኔታ ላይ ሁና ነው። ወያኔ የማይገዛትን አገር እንዳትኖር ለማድረግ እማትወጣው አረንቋ ውስጥ ከመክተት የማይመለስ ኃይል መሆኑን ዛሬ በአምቦ፣ በጉደር፣ በጊምቢ እና መሰል ቦታዎች በተግባር እያስመሰከረ ነው።

የኢትዮጵያ ሕዝብ በታሪኩ ለመጀመሪያ ጊዜ እውነተኛ ፍላጎቱን የመግለጽ አንፃራዊ ነፃነት አግኝቶ የነበረበት የግንቦት 7 ቀን 1997 ዓ.ም. ምርጫን ስናስብ ዛሬ ያለንበት ሁኔታ መመዘናችን አይቀርም። ያኔ ለአብዛኛው የኢትዮጵያ ሕዝብ እንደ እጁ መዳፍ ቀርባ ትታየው የነበረችው ድል እስከዛሬ አልጨበጣትም። ትግሉ ግን ቀጥሏል። የዛሬው ትግላችን የኢትዮጵያ ሕዝብ ከያኔው በበለጠ ከታሪክና ከራስዋ ጋር የታረቀች አገር የመመሥረትን ርዕይ አስፈላጊነት ላይ ትኩረት መስጠትን የሚጠይቅ ሆኗል።

ወያኔ ከተፈጠረበት ጊዜ ጀምሮ ለአለፉት አርባ ዓመታት ሲያብላላው የቆየው፤ በመንግሥት ሥልጣን በቆየባቸው ሃያ ሶስት ዓመታት ውስጥ ደግሞ በፓሊሲ ደረጃ ሲያስፈጽመው የቆየውን የዘር ፓለቲካ አስከፊ ውጤት አሁን እየታየ ነው። ይህ የዘር ፓለቲካ ራሱ ወያኔን ያጠፋዋል። ችግሩ ግን የዘር ፓለቲካ ወያኔን ነጥሎ አያጠፋም፤ ከወያኔ ጋር አገራችንንም ሊያጠፋ ይችላል። ከሁሉም በላይ አሳሳቢው ጉዳይ ደግሞ የዘር ፓለቲካ የበርካታ ኢትዮጵያዊያንን ሕይወት አደጋ ላይ ሊጥል ይችላል። በጎረቤት አገራት ውስጥ ያየነውን ዓይነት የእርስ በርስ እልቂት ወደ አገራችን ለማምጣት ህወሓትና ኦህዴድ ተግተው እየሠሩ ነው። ሌሎች የወያኔ ተቀጥላ ድርጅቶችም የዚህ ትልቅ የጥፋት ፕሮጀክት አካል ናቸው። ( ወደ ገጽ 4 ዞሯል )

## የእንግሊዙ ጋማ ኢንተርናሺናል የስለላ ሶፍት ዌር ለመንግስታትት በማቀበሉ ሀላፊነት መውሰድ እንደሚኖርበት ተወሰነ

አምባገነኑ ገዥ ፋሽስት ወያኔ በሀገር ውስጥም ሆነ በውጭ የሚገኙ የነጻነት ታጋዮችን፣ የመብት ተሟጋጮችንና ጋዜጠኞችን እንቅስቃሴ በቅርበት ለመከታተል ይረዳው ዘንድ ከድሃው ሕዝባችን አፍ በሚነጠቀው ገንዘብ በከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ ፊን ፊሸር የተሰኘ የስለላ ሶፍት ዌር በእንግሊዝ ሀገር ከሚገኘውና ጋማ ኢንተርናሽናል ከሚባለው ኢንዱስትሪ ገዝቶ በማስገባት ስለላውን በማጧጧፍ ላይ እንዳለ ተደርሶበት መጋለጡ አይዘነጋም። በዚህ መሰረትም የተለያዩ ቴክኖሎጂዎችን የሚያመርቱ ኢንዱስትሪዎች ግልጽነትና ተጠያቂነት ሊኖራቸው ይገባል የሚል ዘመቻ ፕራይቬሲ ኢንተርናሽናል በተሰኘው ተቋም አማካኝነት ሲካሄድ እንደነበርም ይታወሳል።

ፕራይቬሲ ኢንተርናሽናል የተባለው ዜጎችን ከመንግስታዊ ስለላ ለመታደግ የተቋቋመው ድርጅት የእንግሊዝ የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣንን ከሶ አስደሳች የፍርድ ውሳኔ ማግኘቱን ገልጿል።ጋማ ኩባንያን ፊን ፊሸር እየተባለ የሚጠራውን የኮምፒዩተርና የስልክ የመረጃ መጥለፊያ ሶፍት ዌር እንደ ኢትዮጵያ ላሉ ሰብአዊ መብቶችን ለሚጥሱ አገሮች መሸጡ በካናዳው ሲትዝን ላብ ላብራቶሪ መረጋጋጡን ተከትሎ ፕራይቬሲ ኢንተርናሽናል በአገር ውስጥ ገቢና ጉምሩክ መስሪያ ቤት ላይ ክስ መመስረቱ ይታወቃል። እንግሊዝ የአገር ውስጥ ገቢ መስሪያ ቤት ከአገሪቱ የሚወጡ ምርቶች በቂ ቁጥጥር ሳይደረግባቸው እንዲወጣ ፈቃድ ሰጥቷል በሚል ነው ( ወደ ገጽ 2 ዞሯል )

## ግንቦት 7 ሕዝባዊ ሃይል ላለፉት ሶስት ወራት ያሰለጠናቸውን የአራተኛ ዙር ታጋዮችን አስመረቀ

የኢትዮጵያዊያንን ስቃይና መከራ ሊያቅብና እንባቸውን ሊየብስ፤ ሀገራችን ኢትዮጵያ በጎጠኛው ሕወሃት የደረሰባትንና እየደረሰባት ያለውን ውርደት ወደ ክብር ለመለወጥና የናቋትና ያዋረዷት በፍትህ ሚዛን ላይ እንዲቀመጡና ፍርዳቸውን እንዲያገኙ ለማድረግ ዓላማየ ብሎ ምሎ ዱሩ ቤቴ ካለ ገና ሁለት ዓመት እንኳ ያልሞላው ግንቦት 7 ሕዝባዊ ሃይል በቃሉ መሰረት አራተኛውን ዙር የታጋዮች የምረቃ በአል ሚያዚያ 26 2006 ዓ/ም ጥሪ የተደረገላቸው የክብር እንግዶች በተገኙበት ማክበሩን አስታወቀ። ይህ የአራተኛው ዙር ስልጠና በሰልጣኞች ቁጥርም ሆነ በስልጠናው ጥንካሬ ካለፉት ሶስት ዙሮች በእጅጉ የተለየ እንደነበር የተገለጸ ሲሆን በአሁኑ ሰአት ያለውን የሀገሪቱን ነባራዊ ሁኔታ ያገናዘበና ወቅቱ የሚፈልገውን ቴክኖሎጅ በመጠቀም መረጃን መቀበልና ማስተላለፍን የጨመረም እንደነበር ተያይዞ ተጠቅሷል።

በሀገር ውስጥ ፋሽስት ወያኔ እያደረሰው ባለው መረን የወጣ ግፍ የተበሳጩና ሁሉም ልክ እንዳለው ለማሳየት ቆርጠው የተሰለፉት እነዚህ ምሩቅ ታጋዮች ከወታደራዊው ስልጠና በተጨማሪ የፖለቲካ፣ መረጃና ደህንነት እንዲሁም ሌሎችንም ተያያዥ ክህሎቶችን በበቂ ሁኔታ እንደቀሰሙም ተጠቁሟል። ስልጠናው ታጋዮቹ ወደፊት ከሚያጋጥማቸው ጠንካራ ፈተናና ከሚሰለፉበት ጥብቅ ግዳጅ አንጻር በቀላሉ ተስፋ እንዳይቆርጡ ለማድረግ በአካልም ሆነ በመንፈስ ዝግጁ እንደሚያደርጋቸው የተገለጸ ሲሆን የተጀመረው ሕዝባዊ ትግል በግለሰብ ደረጃ ሳይሆን በጋራና በተቀነባበረ ሃይል ለድል እንደሚበቃና ይህን የጋራ ሃይል በጠነካራ እጆች ላይ ላመስቀመጥም የተሰጠው ስልጠና ከበቂ በላይ ነበር ተብሏል። ( ወደ ገጽ 2 ዞሯል )

## የደቡብ ሱዳን ፕሬዚደንት ሳልቫ ኪርና ተቀናቃኛቸው ሪክ ማ ቻር ታርቅን ያልነዉ የእስር ዛቻዉን ፈርተን ነዉ አሉ

የሰብአዊ መብት ተሟጋቾችን፣ የተቃዋሚ ፓርቲ አመራሮችንና ተቺ ጋዜተኖችን በየምክኒያቱ በማሰር ይቅርታ ካልጠየቃችሁኝ አልፈታችሁም የሚለው የምስራቅ አፍሪካው ማፍያ ቡድን ህወሃት፤ በምስራቅ አፍሪካ አይደፈሬ የአሜሪካ ቀኝ እጅ ነኝ እያለ አፈና እስርና ግርፋት ሸሽተው በጎረቤት ሀገሮች የተጠለሉትን ምስኪን ኢጥዮጵያዊያንን አሳዶና አፍኖ በማምጣት በእስር እያማቀቀና አንዳንዶችንም በግድያ በመቅጣት የማፍያ ስራውን በዓለም ፊት እየከወነ ያለው ሕወሃት፤ ጠንካራ ኢትዮጵያዊያንን አእምራቸውን ለማላሸቅና ተስፋቸውን ለማጨለም ወንጀል መሰል የውሸት ድራማ እንዲሰሩ በማስገደድ ወይም ራሱ በማዘጋጀትና በማስረጃነት ፍርድ ቤት በማቅረብ የሚከሰው ማፍያው ሕወሃት ይህ ሁሉ አልበቃው ብሎ የማፍያ ስራውን በመቀጠል የደቡብ ሱዳን ፕሬዚዳንት ሳልቫ ኪርንና ተቀናቃኛቸውን ሪክ ማቻርን ስምምነቱን ካልፈረሙ እዚሁ አስሮ እንደሚያስቀምጣቸው በማስፈራራት በተላላኪው ሃይለማሪያም ደሳለኝ በኩል ማስፈራራቱ ተጋለጠ።

የደቡብ ሱዳን ፕሬዚዳንት ሳልቫ ኪር ባደባባይ ለሕዝባቸው እንደገለጹት፣ እሳቸውም ሆኑ ተቀናቃኛቸው ሪክ ማቻር በአዲስ አበባ ላለመታሰር ስንል ያላመንበትን ስምምነት ፈርመናል ብለዋል። “ለሪክ ካንድ ቀን ቀደም ብሎ ለኔ ደግሞ በነጋታው ይህን ሁለታችንም የማናምንበትን ስምምነት ካልፈረምን ሀገራችን ልንገባ እንደማንችል፤ እዚሁ በአዲስ አበባ ( ወደ ገጽ 3 ዞሯል )

## የወያኔ ዘረኞች ኦሮሚያን ህዝባዊ ተቃውሞ የብሄር አጀንዳ ለማድረግ እየተሯሯጡ መሆናቸዉ ተጋለጠ

በዘራፊው የህወሓት ቡድን መሪነትና በኦሮሚያው የፋሽስቱ የጥፋት ክንፍ ኦህዴድ አስፈጻሚነት አዲስ አበባን ለማስፋት በሚል የተነደፈውን የመሬት ዘረፋ ዕቅድ በተለይ በኦሮሚያ ክልል ከፍተኛ የህዝብ ተቃውሞ ማስነሳቱን ተከትሎ ለተቃውሞ የወጡ ዜጎች በአደባባይ አሁንም ድረስ በወያኔው የአጋዚ ጦር በጥይት ተቆልተው እየተገደሉ ሲሆን ይህ አልበቃ ያለው የፋሽስት አገዛዝ ተቃውሞውን ህዝብን ከህዝብ ለማፋጀት እየተጠቀመበት እንደሆነ የውስጥ ምንጮቻችን ከላኩልን መረጃ ለማወቅ ተችሏል። ነፍሰ በላው የህወሓት ቡድን ያሰማራቸው የኦህዴድ የጥፋት ቅጥረኞች የተቃውሞን የትኩረት አቅጣጫ ለማስቀየር ከጉዳዩ ጋር ተያያዥነት የሌለውን የብሄር አጀንዳ በማንሳት ብሄሮች በተለይም ለዘመናት ተፋቅረውና ተዋደው እንዲሁም በደም ተሳስረው በአካባቢው የሚኖሩትን የአማራ ብሄረሰብ ከኦሮሞ ብሄረሰብ ጋር እርስ በርስ እንዲጣሉ ከፍተኛ ጥረት በማድረግ ላይ መሆናቸው ታውቋል።

እንደ ምንጮቻችን ዘገባ በተለይ የተቃውሞ ማዕከላት በሆኑ ዩኒቨርስቲዎች ተብሎ እነዚሁን ብሄረሰቦች ሊጋጩ የሚችሉ ( ወደ ገጽ 2 ዞሯል )

## ትኩረት በህወሓት፣ አህዴድ፣ ብአዴንና ደህዴድ ላይ ይሁን!!!

ዛሬ አገራችን ኢትዮጵያ መንታ መንገድ ላይ ትገኛለች። በአንድ በኩል ህወሓት እና አገልጋይ ድርጅቶቹ በተለይም አህዴድ፣ ብአዴንና ደህዴድ የተነሳባቸው ሕዝባዊ ተቃዉሞ ለመሸፈን የሕዝብ ለሕዝብ ጠብ ለመጫር የተቻላቸውን ሁሉ እያደረጉ ነው። በየተገኘው አጋጣሚ ሁሉ ዘርን መሠረት ያደረጉ ስድቦች፣ ዘለፋዎችና ጥቃቶች እንዲኖሩ በካድሬዎቻቸውና በቅጥረኞች አማካይነት እየጣሩ ነው። በዚህ እኩይ ተግባር ውስጥ ባለማወቅ በስሜት ብቻ የሚነዱ የወያኔ ደጋፊ ያልሆኑ ወገኖችም እየተሳተፉበት ነው። በሌላ በኩል ደግሞ በዘውግም ይሁን በአገር ደረጃ የተደራጁ የፓለቲካ ድርጅቶች መሪዎች የጋራ ጠላቶቻችን ወያኔና ግብረአበሮቹ ስለመሆናቸው የጠራ አቋም እየያዙ ነው። ወያኔና ግብረአበሮቹን ለማስወገድ በጋራ መታገል የሚያስፈልግ መሆኑ እና ከወያኔ አገዛዝ በኋላ በእኩልነት ላይ የተመሠረተ አገር የመገንባት የጋራ ኃላፊነት ያለብን መሆኑ ሰፊ ግንዛቤ እያገኘ መጥቷል።

ይህ መንታ መንገድ በሁሉም ቦታ በባሰ ኦሮሚያ ውስጥ ጎልቶ እየታየ ነው። በኦሮሚያ አካባቢዎች የሚደርሰው ጥቃትና መፈናቀል ያስቆጫቸው ወጣቶች የሚያደርጉት ፍትሃዊ ተቃውሞ ቀጥሏል። በአምቦ፣ በነቀምት፣ በጊምቢ፣ በሀረር፣ እና ሌሎችም አካባቢዎች በተለይም የዩኒቨርስቲ ተማሪዎች ሥርዓቱን በመቃወማቸው ከፍተኛ ጥቃት እየደረሰባቸው ነው። በመቶዎች የሚቆጠሩ ሕይወታቸውን አጥተዋል፤ በሺዎች የሚቆጠሩ ታስረዋል። በእነዚህ ቦታዎች ሁሉ የእንተባበር ጥሪዎች ጎልተው እየተሰሙ ነው። በኦሮሚያ በሚገኙ ዩኒቨርስቲዎች የሌሎች አካባቢዎች ተማሪዎች ከጎናቸው እንዲቆሙ የኦሮሞ ተማሪዎች ተደጋጋሚ ጥሪዎችን አቅርበዋል። የሌሎች አካባቢዎች ተማሪዎችም ከኦሮሞ ወንድሞቻቸውና እህቶቻቸው ጎን ቆመዋል። ይህ ተስፋ የሚሰጥ እና መበረታታት ያለበት ነገር ነው። ሆኖም ግን ከዚሁ ጎን ለጎን ህወሓትና አህዴድ የሕዝቡን ጥያቄ ወደ ዘር ግጭት ለማዞር እየሠሩ ነው። በተማሪዎች መፈክሮች ውስጥ ዘርን ለይተው የሚያንቋንሽሹ መልዕክቶች ሰርገው እንዲገቡ እየተደረገ ነው። ኦሮሞ ባልሆኑ በተለይም በአማራ ተወላጆች ላይ ጥቃት እየደረሰ ነው። የወያኔ ጆሮ ጠቢዎችና ካድሬዎች በስሜት የተገፋፉ ወጣቶችን ወደ ዘር ግጭት እየመሯቸው ነው። ይህ እጅግ አሳሳቢና በአስቸኳይ መቆም የሚኖርበት ነገር ነው።

ከመንታ መንገዶቹ ለአገርና ለወገን እንዲሁም ለወደፊቱ ትውልድ ደህንነት የሚበጀውን የመረዳዳት፣ የመደጋገፍ እና የመተባበርን መንገድ መርጠን እርምጃችንን ካላፋጠንን አሁን የደረስንበት ደረጃ እጅግ አስጊ ነው። ማሰብ፣ ማስተዋል እና ጠላትን መለየት በሚያፈልግበት ወሳኝ ወቅት ላይ ነው የምንገኘው። ድሃ አማራ ለድሃ ኦሮሞ ወገኑ ብቻ ሳይሆን የትግል አጋሩ ነው። አህዴድ ውስጥ ያሉ የወያኔ አገልጋዮች ደግሞ ኦሮሞች ስለሆኑ የድሃ ኦሮሞ ወዳጆች አይደሉም። እነሱ የወያኔ ተቀጥላዎች ናቸው። የትውልድ መንደራቸውን ሳይቀር አዘርፈው የሚዘርፉ ስግብግቦች ናቸው።

የኦሮሞ ሕዝብ ትግል በወያኔ እና ተቀጥላዎቹ ድርጅቶች እንጂ በአማራና በኦሮሞ ወይም በኦሮሞና በትግሬ ሕዝብ መካከል አይደለም። የአማራ ሕዝብ ትግል በወያኔ እና ተቀጥላዎቹ ድርጅቶች እንጂ ከማንኛውም አካባቢ ሕዝብ ጋር አይደለም። ወደ እርስ በርስ ቅራኔ ሊዘፍቁን የሚፍጨረጨሩትን ህወሓት፣ አህዴድ፣ ብአዴንና ደህዴድን ከሕዝብ መነጠል መቻል አለብን። እዚህ እኩይ ኃይሎች ሥልጣን ላይ እስካሉ ድረስ ፍትህና ሰላም ማግኘት አንችልም። እዚህ እኩይ ኃይሎች እርስ በርሳችን ሊያጫርሱን እየሠሩ መሆኑን አውቀን ኃይላችንን በማስተባበር እንመክታቸው።

ግንቦት 7 የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ በማናቸውም የኢትዮጵያ ግዛት የሚደርስን የሰብዓዊ መብት ጥሰትን በፍጹም ቁርጠኝነት በጋራ እንታገል፤ በስሜት ከተሞሉና ለእርስ በርስ ግጭቶች ከሚዳርጉ ነገሮች እንቆጠብ፤ አርቆ አስተዋይነትና ታጋሽነት በተላበሰ መንገድ የጋራ ጠላቶቻችን በሆኑትን በህወሓት እና አጫፋሪዎቹ አህዴድ፣ ብአዴን እና ደህዴድ ላይ በጋራ እንነሳ ሲል ለመላው ኢትዮጵያ ሕዝብ ጥሪ ያደርጋል።

**ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ!!!**

---

## ግንቦት 7 ሕዝባዊ ሃይል ላለፉት ሶስት ወራት ያሰለጠናቸውን

. . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

ግንቦት 7 ሕዝባዊ ሃይል በሀገር ውስጥ እንደማእበል እየገነፈለ ያለውን የአታግሉን የሕዝብ ጣያቄ በተደራጀና በተቀነባበረ መንገድ በተገቢው መልኩ ለማስተናገድ እንዲችል እንደ ድርጅት ከመቼው በላይ ራሱን እያደራጀና እያጠነከረ እንደሚገኝና ምቹ አታጋይ ተቋም ሆኖ ለመውጣት ሌት ተቀን እየደከመ መሆኑም ተያይዞ ተጠቅሷል። በታጋዮች ስልጠና ወቅት የተገኙ አንዳንድ የክብር እንግዶች እንደጠቆሙትም "ባሁኑ ሰአት በሀገር ውስጥ ያለው ሁኔታ ከመቼውም በላይ የተመቻቸ ነው" ካሉ በኋላ "ሕወሃት የሚተማመንበት ወታደሩ እንኳ ቁጥሩ ካልሆነ በቀር ልቡም ሆነ መንፈሱ ከሕዝብ ጋር ነው፤ በሁሉም የሀገሪቱ አቅጣጫዎች እየሆነ ያለው ወያኔ በእርጅና ዘምኑ ማብቂያ ላይ መሆኑን ነው የሚያመለክተው። ስለሆነም በመረጃ መንቀሳቀስና በትብብር መስራት ባጭሩ ለድል ያበቃል። ለዚህ ደግሞ የዛሬ ምሩቅ ታጋዮች ያገኙት ስልጠና ለታሰበው ስኬት የሚያበቃቸው ነው" በማለት ትዝብታቸውን አጠቃለዋል።

በምረቃው ማብቂያ ላይ ራሱን ግንቦት 7 ሕዝባዊ ሃይል ብሎ ከሰየመበት ጊዜ ጀምሮ ለፋሽስት ወያኔ ከፍተኛ ስጋት እንደሆነ በማስረገጥ የጠቆሙት የሕዝባዊ ሃይሉ ሃላፊዎች፤ ከዚህ በፊት ፋሽስት ወያኔ በከፍተኛ ወጭና ጥንቃቄ ሕዝባዊ ሃይሉን ለማፈራረስና ለማትፋት በከፍተኛ ሁኔታ የሰራ ቢሆንም በሕዝባዊ ሃይሉ መረጃና ደህንነት ክፍል መክሸፉን አስታውሰው፤ ዓላማችንን ከዳር ለማድረስና የሕዝባችንን አርነት ለመመለስ ሀገራችንንም ከወያኔ አገዛዝ ነጻ ለማውጣት በምናደርገው ትግል የኢትዮጵያ ሕዝብ ከመቼውም ጊዜ በላይ ከጎናቸው እንዲቆም ጥሪ አስተላለፈዋል። ይህን ታሪካዊ ጥሪ ለመመለስና የሀገርና የትውልድ ጠላት የሆነውን ወያኔ ሕወሃትን ለማስወገድ አብረን እንቁም ሕዝባዊ ሃይላችንንም ተቀላቀሉ ሲሉም ጥሪያቸውን አስተላልፈዋል።

---

## የወያኔ ዘረኞች ኦሮሚያን ህዝባዊ ተቃውሞ የብሄር አጀንዳ . . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

አሉባልታዎችን የሚነዙ ካድሬዎች በብዛት መሰማራታቸው የታወቀ ሲሆን በተለያዩ ተቃውሞ በተቀሰቀሰባቸው የኦሮምያ አካባቢዎችም አህዴድ በቡድን ያደራጃቸው የጥፋት ቅጥረኞች በሌሊት ወደ አማራ ብሄር ተወላጆች ቤት በመላክ ግጭት እንዲያስነሱ እየተደረገ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል። በአሁኑ ጊዜ በተለይም በተቃውሞ እየታመሱ በሚገኙት በምስራቅ እና በምእራብ ወለጋ የወያኔው የጥፋት ክንፍ አህዴድ ያደራጃቸው ቅጥረኛ ወጣቶች የአማርኛ ተናጋሪ ሰዎችን ቤቶች እየመረጡ በሌሊት ከመደብደብ ጀምሮ እስከ ማቃጠል መድረሳቸውን እንዲሁም ንብረቶችን እየዘረፉ እንደሚገኙ ምንጮቻችን አመልክተዋል። ሰዎችም መገደላቸው የታወቀ ሲሆን እጅግ በርካቶች መቁሰላቸውና በከተሞች የሚገኙ ሱቆች፣ መጋዘኖችና ሌሎች የንግድ ቤቶች መቃጠላቸው ታውቋል:: ለሁለቱ ብሄሮች መቃቃር፤ ለሰዎች መገደልና እየደረሰ ላለለው ከፍተኛ የንብረት ውድመት ተጠያቂዎቹ የአህዴድ ቅጥረኛ ካድሬዎች ናቸው በማለት አስተያየቱን ለሬዲዮ ክፍላችን ያደረሰን አንድ የወለጋ ዩኒቨርሲቲ መምህር የኦሮሞ ልሂቃን እየተደረገ ያለውን ነገር በአደባባይ ወጥተው ማውገዝና የኦሮሞ ህዝብ የአገዛዙ የዘር ፖለቲካ መጠቀሚያ እንዳይሆን ማሳወቅና ማስተማር ይኖርባቸዋል በማለት ምክር አዘል አስተያየታቸውን ሰንዝረዋል።

ነፈሰ በላው ህወሃት ከጥፋት ክንፉ አህዴድ ጋር በመሆን የአማራንና የኦሮሞን ብሄሮች በማጋጨት እልቂትን በመፍጠር የአገዛዙን እድሜ ለማርዘም እንደወትሮው ሁሉ ዛሬም ሰይጣናዊ ስራውን እየሰራ ነውና ህዝቡ አስፈላጊውን ጥንቃቄ በማድረግ በትእግስትና በተለመደው የመከባበር ባህሉ ይህን ችግር እንዲያልፈው በዚሁ አጋጣሚ ለማሳሰብ እንወዳለን።

---

## የእንግሊዙ ጋማ ኢንተርናሺናል የስለላ ሶፍት ዌር ለመንግስታትት . . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

ክስ የተመሰረተበት። ፍርድ ቤቱ የአገር ውስጥና የጉምሩክ መስሪያ ቤት አስፈላጊውን መረጃ እንዲሰጥ ውሳኔ አስተላልፏል። ኮምፒተራቸው የተሰለለባቸው ዶ/ር ታደሰ ብሩ ውሳኔው አስደሳች ነው ብለዋል።

ከጉዳዩ ጋር በተያያዘም የግንቦት 7 ንቅናቄ ከፍተኛ አመራር የሆኑት ዶር ታደሰ ብሩን ጨምሮ ሌሎችም በፊን ፊሸር አማካኝነት የደረሰባቸውን የመብት ጥሰት ሲጋልጡ መቆየታቸው የሚታወቅ ሲሆን እንሆ ጥያቄያቸው ፍሬ አፍርቶ እንደ ፊን ፊሸር ያሉ ሚስጥራዊና ባለቤቱ ሳይፈቅድና ሳያውቅ በመግባት ሚስጥር የሚወስዱና የሚሰልሉ መሳሪያዎችን በማምረት በተለይም እንደ ፋሽስት ወያኔ ላሉ ጨቋኝ ገዥዎች አሳልፎ በመሸጡ ጋማ ኢንተርናሽናል ሃላፊነቱን ይወስዳል የሚል ውሳኔ በመሰማቱ ፕራይቬሲ ኢንተርናሽናልን ቸምሮ ለሰው ልጆች መብት መከበር የሚታገሉ ድርጅቶችና ግለሰቦች ደስታቸውን በመግለጽ ላኢ ናቸው ተብሏል።

---

## አኖሌ.....የባህር ዳር ነውር....አምቦ እና ግምቢ

ኢትዮጵያችን አደጋ ላይ ነች። የአደጋዋ ምንጭ ህወሃት እና ህወሃት ነው። ህወሃቶች በአገራችን ላይ የመዘዙት የበቀል ሰይፍ ወደ ሰገባው የሚመለስ አልሆነም። ከበቀል ስሜታቸው ጋር መቶ ዓመት የመንገስ ምኞት አላቸው። ምኞታቸውንም እውን ለማድረግ የንፁሃን ደም ለህወሃቶች መስዋዕት ሆኖ መቅረብ ይኖርበታል። እስከ ዛሬ ብዙ ኦሮሞዎችና አማሮች መሥዋዕት ሁነዋል። የመስዋዕቱ ምንጭ እንዳይደርቅ አሩሲ ላይ አኖሌ ቁሟል።እርሱን ተከትሎ ባህር ዳር "አማራና ኦሮሞ" ኳስ እንዲጫወቱ ሁኖ ነውር የሆኑ ስድቦች እየተነቀሱ ወጥተው በኢቲቭ እንዲተላለፍ ተደረገ። ይሄን ተከትሎ የመሬት ቅርምቱ ተከሰተ። አምቦና ግምቢ ላይ በህወሃት-ኦህዴድ ፊታውራሪነት የንፁሃን ደም በከንቱ ፈሰሶ ህወሃት የለመደውን ምሱን አገኘ።

ህወሃት የአኖሌ ሃውልት እንዲሰራ ሲፈቅድ የሚታየው በዚህ ሃውልት ምክንያት አብረው የኖሩ ህዝቦች ደም ተቃብተው በጠላትነት ሲቆሙ ነው።የአኖሌ ሃውልት በህወሃት-ኦህዴድ እጅ ሁኖ የሚሰብከው አብሮነትን ሳይሆን ልዩነትን ነው። ፍቅርን ሳይሆን ጥላቻን ነው። የአኖሌን ሃውልት የሚመስል ሌላ ሰማይ ጠቀስ ኃውልት በመቀሌ ከተማ ለትውልድ የሚተላለፍ ቂምን እየሰበከ ቁሟል። ስሙንም "የሰማዕታት" ሃውልት ብለው ይጠሩታል። ከአሩሲው አኖሌም ሆነ ከመቀሌው ሠማዕታት ሃውልት ትውልዱ የሚያተርፈው ቂም እና በቀል ነው። እነዚህ ሁለት ኃውልቶች ሠላምን አይሰብኩም፤ አብሮ መኖርን አያስተምሩም። ሃውሎቶቹን ያየ ግማሹ ቂም ይቋጥራል፤ ገሚሱ ይገረማል፤ ሌላውም የአገሪቱን መፃኢ ሁኔታ እያሰበ ይተክዛል። ህወሃቶች እጅግ ብዙ አሰቃቂ፤ አስገራሚ እና አሳዛኝ ነውሮችን በዚያች አገር ላይ መፈፀማቸው የታወቀ ነው።

የአኖሌ ኃውልት ተሠርቶ ከተመረቀ በኋላ በባህር ዳር ከተማ አማራና ኦሮሞ ኳስ እንዲጫወቱ ተደረገ። በዚያ ስቴዲየም ህወሃት-ብአዴን ያሰለጠኗቸው ምናምንቴ ካድሬዎች በኦሮሞዎቹ ላይ የስድብ ናዳ አወረዱ። ስድቡም በቀጥታ በቴሌቭዥን ለህዝቡ እንዲደርስ ሆነ። ይሄን ተመልክተው የሚቆጡ ሌሎች ምናምንቴዎች በህወሃት-ኦህዴዶች ተዘጋጅተው ወደ ህዝቡ መካከል ዘው ብለው ገቡ። የሚያቆማቸውም የመንግስት አካል አልተገኘም።

ይህ በእንዲህ እንዳለ በአዲስ አበባ "ልማት" ሰበብ በዙሪያዋ የሚገኙ ብዙ ገበሬዎች ተፈናቅለው ሜዳ ላይ ሊጣሉ የመሆናቸ ነገር ይናፈስ ጀመር።የሚነፍሰውን ወሬ መንግስት ነኝ የሚለው ቡድን ለህዝቡ ለማስረዳት ፈቃደኛ ሳይሆን በመቅረቱ ዜጎች ተቆጡ። ተማሪዎችም በየትምህት ክፍላቸው የገበሬዎችን ጥያቄ አንግበው ተነሱ። "መሬት ላራሹ" እንደገና ዞሮ መጣ። ህወሃት ከማንም በላይ ለአርሶ አደሩ ቆሜያለው ቢልም እንደ ህወሃት አርሶ አደሩን መሬት አልባ ያደርገ ሥርዓት በኢትዮጵያ ታሪክ አልታየም። የአርሶ አደሩን መሬት ነጥቆ ለባዕዳን በመሸጥ እና አርሶ አደሩን ከነቤተሰቡ ሜዳ ላይ በመበተን ህወሃትን የሚመስለው እስከ ዛሬ አልታየም።

በየትምህርት ተቋማቱ ተማሪዎች "ገበሬ ለምን ይፈናቀላል?" እያሉ መጠየቅ ጀመሩ። ከዚህ ፊትሃዊ ጥያቄ ጀርባ የአማራውን ህዝብ ስጋት ውስጥ የሚከት ነገር አብሮ ብቅ አለ።የገበሬዎች የመፈናቀል ጥያቄ ተረስቶ የተቃጠለው 'የአማራ" ነው የተባለ ሆቴል የኢቲቪን መስኮት ያጨናንቀው ጀመር። በግምቢም የድሃ አማሮች ቤት እየተመረጠ በድንጋይ ይወቀር ጀመር። የንፁሃን አማሮች ደምም በከንቱ ፈሰሰ። እንዲህ ሲሆን ህወሃቶች ከቅጥረኛቸው ኦህዴድ ጋር የደም ፅዋቸውን አንስተው እየተጎነጬ በደስታ ሰከሩ።

የተከበራችሁ ያገራችን ዜጐች !

ከመቼውም ግዜ በከፋ ሁኔታ አገራችን አስቸጋሪ መንግድ ውስጥ ትገኛለች።በየቦታው በብሄሮች መካከል የሚነሳውን ግጭት የሚመራው ህወሃት መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል። ደጋግመን ለማለት እንደሞከርነው ህወሃት የህዝብ ጠላት መሆንን የመረጠ ቡድን ነው። ህወሃት "አማራና ተፈጥሮ የትግራይ ህዝብ ቀንደኛ ጠላቶች ናቸው" ብሎ የሚያምን ቡድን ነው።በዋናነት የአማራን ህዝብ ለማጥፋት ባለፉት ሁለት አስርተ ዓመታት ሳይታክት ሠርቷል። አንድን ህዝብ እንደጠላት የቆጠረ ቡድን ለሌሎች የሰው ልጆች ወዳጅ እንዲሆን የሚያስችል የሞራል ግዴታ ይኖርዋል ለማለት አይቻልም።ስለዚህም ህወሃት የሰው ልጆች ሁሉ ጠላት ነው። ህወሃት ይሄ ነው ተብሎ የሚጠቀስ በጎ ታሪክ ያለው ድርጅት አይደለም። የህወሃት ታሪክ የግዲያ ታሪክ ነው። የህወሃት ታሪክ የዝሪፊያ ታሪክ ነው። የህወት ታሪክ የአገርን ክብር የማዋረድ ታሪክ ነው። ህወሃት ከዚህ የተለየ ታሪክ ያለው ቡድን አይደለም።

ውድ ኢትዮጵያዊያን !

አሁን ከእኛ ከፍ ያለ ትዕግስት፤ አስተዋይነት፤ አርቆ አሳቢነት ይጠበቃል። እኛ እንደ ህወሃቶች ርህራሄ የሌለን ጨካኞች መሆን አይኖርብንም።ህወሃቶች በዘረጉልን መረብ ውስጥ ገብተን እርስ በእርሳችን እንዳንተላለቅ ብርቱ ጥንቃቄ ማድረግ ይኖርብናል። በአምቦ የሆነውን አይተናል።ከግምቢም አሳዛኝ ድምፅ ሰምተናል። ይሄ ግን የህዝብ ፍላጎት ሳይሆን የህወሃት-ኦህዴዶች እቅድ ነው። በባህር ዳር ስቴዲየም የተሰማው ነውረኛ ድምፅ የህዝብ ፍላጎት አይደለም። የህወሃት-ብ አዴኖች እጅ ሥራ ነው። ህወሃቶች በአማራውና በኦሮሞው መካከል የከረረ ግጭት አስነስተው በሚፈሰው የንፁሃን ዜጎች ደም እጃቸውን ታጠበው መቶ ዓመት ከነ ልጅ ልጆቻቸው ሊገዙን ይፈልጋሉ። ይሄ በሁሉም ዘንድ የሚታወቅ እውነት ነው። ይሄ ፍላጎታቻቸው እውን እንዳይሆን ፈጣሪን በመፍራት እና ለእውነት፤ ለፍትህ፤ለእኩልነት እና ለሁላችንም የምትሆን ኢትዮጵያን ለመፍጠር ዓይናችንን ከህወሃቶች ላይ ሳናነሳ በፅናት እንታገል።ኢትዮጵያችን ፈርጀ ብዙ ችግሮች ያሉባት አገር ነች። ከሁሉም ችግሯ የሚልቀው ግን ፍፁም ኃላፊነት የማይሰማቸው አገርን ለመምራት ግዙፍ የሆነ የሞራልም ሆነ የእውቀት ጉድለቶች ያሏቸው ህውሃቶች በአገራችን ጫንቃ ላይ ቁጢጢ ማለታቸው ነው። እነዚህ ቡድኖች አደብ ገዝተው ከህግ በታች መሆንን መልመድ ይኖርባቸዋል። እነርሱ ከህግ በላይ ሁነው ሌሎች ዜግች ከእነርሱ ሥር ሁነው የሚገኝ ልማትም ሆነ ሠላም የለም።

የተከበራችሁ የአገራችን ዜጎች !

ህወሃቶች ለርካሽ የፖለቲካ ጥቅም ሲሉ የሃውዜንን ህዝብ ማስጨፍጨፋቸው የቅርብ ግዜ ትዝታችን ነው። ዛሬም የሚያሰሉት እንዲህ ዓይነቱን ርካሽ ጥቅም ነው። በዚህ ግዜ እኔ ንፁህ ኦሮሞ ነኝ፤ እኔ ንፁህ አማራ ነኝ፤እኔ ከዚህ ነኝ እኔ ከዚያ ነኝ ማለት አይጠቅምም። እንዲህ ለማለት ግዜ አለው።ህወሃቶች የመጨረሻውን ካርድ መዘው ምድሪቷን በደም ሊያጨቀዩ ቆርጠው ተነስተዋል። በህዝቦች መካከል የሚነሳው ግጭትና የሚፈሰው ደም የህወሃቶችን የስልጣን ጥም ለማርካት የሚቀርብ መሥዋዕት ነው። የንፁሃን ዜጎች ደም በከንቱ እንዳይፈስ ከልዩነቶቻችን በላይ አንድ በሚያደርጉን ቁም ነገሮች ላይ እናተኩር። ዓይኖቻችን ልዩነቶቻችንን ለመጠፋፈያነት ለመጠቀም ከሚፈልጉት ህወሃቶች ላይ ሳናነሳ በአንድነት ለእኩልነት፤ ለነፃነት፤ለፍትህ እና ለሁላችንም የምትሆን አገር ለመፍጠር ሳናቅማማ እንታገል። ህወሃት እያለ ለሁላችንም የምትሆን አገር እንደማትኖር የታወቀ ነው።ለሁላችንም የምትሆን አገር እንድትፈጠር በየትኛውም መንገድ ህወሃት መወገድ ይኖርበታል።

አኖሌ...ባህር ዳር....አምቦና ግምቢ ላይ የሰማናቸው ድምፆች የጥፋት ድምፆች ናቸው። በዚህ ሁኔታ ለፈሰሰው ደም ተጠያቂው "መንግስት" ነኝ የሚለው ህወሃት-ኢህአዴግ ነው። የሌላ የማንም እጅ የለበትም። የንፁሃንን ህይወት ቀጥፎ በሠላም ስልጣን ላይ መቆየት ፈፅሞ አይቻልም። ህወሃት የብዙ የትግራይ ልጆችን መሠዋዕትነት ከንቱ ያስቀረ የጨካኞችና የነፍሰ ገዳዮች ስብስብ ሁኗል። ይሄን ነፍሰ ገዳይና ጨካኝ ቡድን ከተቆናጠጠበት ወንበር ላይ ለማውረድ ቆርጠን በምንችለው ሁሉ እየሠራን ነው። ዘወትር እንደምንለው ሁላችሁም በያላችሁበት፤ በምትችሉት መንገድ ሁሉ ለፍትህ፤ ለነፃነትና ለእኩልነት ዘብ የምትቆሙ ሁኑ እንጂ ህወሃቶች ባዘጋጁት የመተላለቂያ መርብ ውስጥ የምትወድቁ ደካሞች አትሁኑ።

**ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ !**

## የደቡብ ሱዳን ፕሬዚደንት ሳልቫ ኪርና ተቀናቃኛቸው ሪክ ማ ቻር

. . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

በእስር እንደምንማቅቅ ሃይለማሪያም ደሳለኝ አስጠነቀቀኝ" የሚሉት የደቡብ ሱዳን ብሬዚዳንት ሳልቫ ኪር፤ እኛ ከአወያዮች ጋር ከመገናኘታችን በፊት ተጨማሪ ሰአት እየጠየቀ ሃይለማሪያም ደሳለኝ ሊያስፈራራኝ ሞከረ" የሚሉት ፕሬዚዳንቱ "ይህማ በጣም ጥሩ ነው ምክንያቱም እኔም ሳልደክም ባንተ እስር ቤት ሆኜ ጥሩ ጥሩ ምግብ እመገባለሁ ማለት ነው አልኩት" በማለት የወያኔን የማፍያ ስራ ለታሪክ በሕዝባቸው ፊት ባደባባይ አጋልጠዋል።

በዚህ የተነሳም ድሮም ያለስምምነት በፋሽስት ወያኔ ፋሽስታዊ ማስፈራሪያና በእስር ፍራቻ ብቻ የተፈረመ ነበርና ሰምምነቱ ተፈረመ ከተባለ ሁለት ቀን ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ስምምነቱ ፈርሱ ሁለቱ ሃይሎች ዳግም ወደ ጦርነት መግባታቸው ታውቋል። ከዚህ በፊትም ባሁኑ ሰአት በሂዎት በሌሉት የሶማሊያ የሽግግር መንግስት ፕሬዚዳንት በነበሩትና በበታች ሹማምንቶቻቸው መካከል ተመሳሳይ ማስፈራራትና እኔ የምላችሁን ብቻ ተቀበሉ አይነት አካሄድ የተከተለው ሕወሃት ብጥብጡን አርዝሞ ለከፍተኛ የሂዎትና ሀብት ውድመት እንደዳረጋቸው አይዘነጋም።

## የጉጅሌው ወያኔ አገዛዝ በሐረር 22 ነጋዴዎችን በሽብረተኝነት ወንጀል መክሰሱ ተሰማ

በሐረር ከተማ ከወራት በፊት የተነሳውን ህዝባዊ ተቃውሞ ተከትሎ፣ የንግድ ድርጅታቸው በፋሽስቱ ወያኔ ቅጥረኞች የተቃጠለባቸው 22 ነጋዴዎች ሁከት አስነስታችኋል በማለት የተከፈተባቸው ክስ ወደ ሽብርተኝነት በመለወጡ፣ ዋስትና ተከልክለው በእስር ቤት እየተሰቃዩ እንደሚገኙ የሐረሩ ዘጋቢያችን ካደረሰን መረጃ ለማወቅ ችለናል።

የጉጅሌው ወያኔ የካንጋሮ ፍርድ ቤት ነጋዴዎች በዋስ እንዲለቀቁ ውሳኔ አሳልፎ የነበረ ቢሆንም፣ የጉጅሌው ወያኔ ቅጥረኞች ፖሊስና አቃቢ ህግ ክሱን ወደ አሸባሪነት በመለወጣቸው ነጋዴዎቹ ከእስር ቤት እንዳይወጡ ተደርጓል። ከእስረኞቹ መካከል 2ቱ ሴቶች ሲሆኑ አንደኛዋ በድብደባ ወቅት ማህጸኗ አካባቢ በመረገጡዋ በከፍተኛ ህመም እየተሰቃየች መሆኑን ዘጋቢያችን ገልጿል።

ዘጋቢያችን እንደገለጸው በእስር ላይ የሚገኙት ነጋዴዎች በፋሽስቱ ወያኔ አቀናባሪነት ድርጅታቸው ተቃጥሎባቸው ለኪሳራ መዳረጋቸው ሳያንስ አሁን ደግሞ በሽብረተኝነት ተከሰው የዋስትና መብት መከልከላቸው በአገሪቱ ውስጥ የጉጅሌው ወያኔ አገዛዝ ያንሰራፋውን ስርአት አልበኝነት ያሳያል በማለት አስተያየት ሰጪዎች ጠቅሰ ዘግቧል።

በሌላ ዜና የጅቡቲ መንግስት 30 ኢትዮጵያውያን ስደተኞችን ለፋሽስቱ ወያኔ የጸጥታ ሃይሎች አሳልፎ መስጠቱ ታውቋል። የኦጋዴን ነፃ አውጭ ግንባር እንዳሳወቀው እርምጃው የተወሰደው በጅቡቲ የኦጋዴን ተወላጅ የዳያስፖራ አባላት በኦሮሞ ተወላጅ ተማሪዎች ላይ የደረሰውን ጭካኔ የተሞላበት እርምጃ ካወገዙ በሁዋላ ነው። የጅቡቲ መንግስት የኦጋዴን ተወላጅ ስደተኞችን ለፋሽስቱ ወያኔ አሳልፎ ሲሰጥ የአሁኑ ለ6ኛ መሆኑን የገለፀው ግንባሩ የአለማቀፉ ማህበረሰብ የጅቡቲን ድረጊት እንዲያወግዝ ጥሪ አቅርቧል።

## ወያኔ የአዲስ አበባን ማስተር ፕላን የተቃወሙ የኦህዴድ አባላት እያደነ መሆኑ ተሰማ

አበባ ማስተር ፕላን ጋር በተያያዘ የህወሃት አጀንዳ ነው በማለት ተቃውሞ ሲያሰሙ የነበሩትን የኦህዴድ አባላት ለማሰር እንቅስቃሴ መጀመሩን ከኦህዴድ ምንጮች የደረሰን ዜና አመለከተ። ለደህንነታቸው ሲባል ስማቸው እንዳይገለጥ የፈለጉት እነዚህ አባላት እንደተናገሩት፣ ድርጅቱ አዲሱን የአዲስ አበባ ፕላን በተመለከተ አባላቱ እንዲወያዩበት ቢያስደርግም፣ በውይይቱ ወቅት የተቃውሞ ሃሳባቸውን ሲያሰሙ የነበሩትን ሰዎች ማሰር ተጀምሯል። በርኬታ የድርጅቱአባሎች ደግሞ ከእስራት ለመሸሽ መደበቃቸው ታውቋል።

ኦህዴድ የህወሃት ደጋፊና የህወሃት ተቃዋሚ በሚል ከሁለት መከፈሉን ተከትሎ የህወሃት ደጋፊው ወገን ደጋፊ ያልሆነውን ወገን እያሳደደው መሆኑን ምንጮች አክለው ገልጸዋል። ይህ በእንዲህ እንዳለ በተለያዩ የኦሮምያ አካባቢዎች ህዝብን ከህዝብ ለማጋጨት የሚደረገው ጥረት፣ የህወሃት ደጋፊ በሆኑ የኦህዴድ አባላት ተጠናክሮ ቀጥሎአል። ኢህአዴግ ከአዲስ አበባ ማስተር ፕላን ጋር በተያያዘ የተነሳበትን ተቃውሞ የትኩረት አቅጣጫ ለማስቀየር ከጉዳዩ ጋር ተያያዥነት የሌለውን የብሄር አጀንዳ በማንሳት ብሄሮች እርስ በርስ እንዲጣሉ ከፍተኛ ጥረት በማድረግ ላይ መሆኑን አባሎቹ ተናግረዋል።

በዩኒቨርስቲዎች ሆን ተብሎ አሉባልታ የሚነዙ ካድሬዎች መሰማራታቸውን እንዲሁም በተለያዩ አካባቢዎች በቡድን የተደራጁ ስራ አጥ ወጣቶችንበሌሊት ወደ ሌሎች ብሄር ተወላጆች ቤት በመላክ ግጭት እንዲያነሱ በኳድሬዉች ግፊት እየተደረገመሆኑን እነዚህ ወገኖች አክለው ገልጸዋል።በምስራቅ እና በምእራብ ወለጋ ኦህዴድ ያደራጃቸው ወጣቶች የሰዎችን ቤቶች እየመረጡ በሌሊት ከመደብደብ ጀምሮ እስከ ማቃጠል መድረሳቸውን እንዲሁም ንብረቶችን እየዘረፉ እንደሚገኙ የሚናገሩት አባሎቹ፣ ህዝቡ በትእግስትና በተለመደው የመከባበር ባህሉ ይህን ችግር እንዲያልፈው አሳስበዋል።

በሌላ ዜና ደግሞ በድሬዳዋ ዩኒቨርስቲ የተነሳውን ተቃውሞ ተከትሎ በቁጥጥር ስር ውለው የነበሩ ከመቶ በላይ ተማሪዎች ሲለቀቁ፣ 40 ተማሪዎች ግን አመጹን ከቅስቅሳችሁዋል በሚል በእስር ላይ እንዲቆዩና ምርምራ እንዲደረግባቸው ፖሊስ መወሰኑ ታውቋል። በተመሳሳይ ዜና ከሃሮማያ ዩኒቨርስቲ የወጡትን ተማሪዎች አስጠግተው የነበሩ ቤተክርስቲያኖች፣ ተማሪዎቹን እንዲያስወጡ _ክልሉን በሚመራው የምስራቅ እዝ ወታደራዊ አዛዦች ትእዛዝ ተሰጥቷቸው እንደነበር የደረሰን መረጃ ያመለክታል። ማንነታቸውን ያልገለጹ የምስራቅ እዝ ባለስልጣናት ቤተክርስቲያኑዋ በአስቸኳይ ተማሪዎችን እንድታስወጣ ትእዛዝ ከሰጡ በሁዋላ ተማሪዎቹንሽራ በለበሱ መኪኖች ተጭነው መውሰዳቸውን ጉዳዩን በቅርበት ከሚከታተሉ ወገኖች የደረሰን መረጃ ያመለክታል። በሃሮማያ ዩኒቨርስቲ ሰኞ እለት ትምህርት ቢጀመርም በግቢው የሚገኙ ተማሪዎች ቁጥር አሁንም እጅግ አነስተኛ ነው።በኦሮምያ ክልል ያለውን የጸጥታ ችግር በተመለከተ የክልሉን ፖሊስ ለማነጋገር ተደጋጋሚ ሙከራ ብናደርግም አልተሳካልንም።

## ወያኔ ዞን ዘጠኝ ጦማሪያንና ጋዜጠኞችን

## ዝክር ለግንቦት 7 1997 እና ለግንቦት 7 ቀን 2000 ዓ.ም.

. . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

የግንቦት 7 1997ቱ ብሩህ ተስፋ በፋሺስቱ ወያኔ የግፍ አፈና ሲጨልም፤ ያ ተስፋ እንዲያንሠራራ በግንቦት 7 2000 ዓ.ም. የተቋቋመው ግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ ዛሬ የኢትዮጵያን ተስፋ ለማጨለም ከተነሱ ኃይሎች በተፃራሪ በመቆም የሕዝብና የአገር አለኝታነቱ ማረጋገጥ ይኖርበታል።

በዚህም ምክንያት፣ በዚህ ወሳኝ ወቅት የግንቦት 7 አባላትና ደጋፊዎች የሆንን ሁሉ በከፍተኛ የኃላፊነት ስሜት መንቀሳቀስ ይኖርብናል። በግራም ይሁን በቀኝ ያለ ጽንፈኝነት አገራችን አይጠቅምም፤ የምንመኛትን ኢትዮጵያ አያመጣልንም። ሕዝባችንና አገራችንን ከዚህ አረንቋ ማውጣት የሚቻለው የአንድነትና የእኩልነት ፖለቲካን አሸናፊ ማድረግ ስንችል ነው።

በአሁኑ የኢትዮጵያ ፖለቲካ ለሀገራችን የሚጠቅማትና ትክክለኛ ነው ብለን የምናምነው ለኢትዮጵያ ሉዓላዊነት የሚታገል፤ የተለያዩ የኅብረሰተሰብ ክፍሎች በመሰላቸው መንገድ ለመደራጀት መብታቸው እውቅና የሚሰጥ፤ በኢትዮጵያ የሚገኙ ማኅበረሰቦች በሙሉ በእኩልነት የሚስተናገዱበት ሥርዓትን የሚያልም፤ መሰማማት፣ መቻቻል እና ከዚያም አልፎ መተጋገዝ ያለበት የኢኮኖሚና የፖለቲካ ሥርዓት እንዲኖር የሚታገል፤ የእምነቶች እኩልነትን የሚያከብር፤ በታሪክ ውስጥ የተፈፀሙ በደሎችን መርምሮ ማኅበራዊ እርቅ ለመፍጠር ፍላጎት ያለው ፖለቲካ ነው።

ይህ ዓይነቱ የአንድነትና የእኩልነት ፖለቲካ በአሸናፊነት እንዲወጣ ማድረግ ይቻላል ብሎ ግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ ያምናል። ይህ ለሁላችንም የሚበጀው ፖለቲካ አሸናፊ ለማድረግ የሚከተሉትን መፈፀም ይጠበቅብናል።

1. በማንኛውም የኢትዮጵያ ክፍል ውስጥ የሚደርስ የሰብዓዊ መብት ጥሰት በፍጹም የማንታገስ መሆኑን ማመንና በተግባሮቻችንም ይህንኑ መግለጽ፤
2. ኢትዮጵያ ከገባችበት ችግር መውጫው መንገድ ወያኔን ማስወገድና በምትኩ የዜጎችን እኩልነት የሚያረጋግጥ፣ ሕዝብን ከሕዝብ የሚያስታርቅና የሚያስተሳስር መንግሥት መመሥረት መሆኑን ማመንና በተግባሮቻችን ማሳየት፤
3. የኢትዮጵያ ዋነኛ ጠላቶች ወያኔ እና ተቀጥላዎቹ፣ በተለይም ህወሓት፣ ኦህዴድ፣ ብአዴን እና ደህዴድ መሆናቸውን በማመን ትኩረታችንን ነቀሎ ወደሌላ ከሚወስዱ አስተሳሰቦችና ድርጊቶች መቆጠብ፤
4. በብሔር ከተደራጁ ኃይሎች ጋር በሚለያዩን ነገሮች ላይ ሳይሆን በሚያስተሳስሩን ጉዳዮች ላይ በማተኮር የወያኔን የከፋፍለህ ግዛ አጀንዳ ማክሸፍ፤
5. በስሜትከተሞሉ የአጭር ጊዜ እይታዎች ለእርስ በርስ ግጭቶች ከሚዳርጉ አስተሳሰቦችና ተግባራት መቆጠብ፤ እና
6. እርቅ አስተዋይነትና ታጋሽነት በተላበሰ መንገድ ለኢትዮጵያ ሕዝብና ለኢትዮጵያ ደህንነት፣ለፍትህና ለነፃነት በግንባር ቀደምትነት መቆም፤

የግንቦት 7 ንቅናቄ አባላትና ደጋፊዎች ከላይ የተዘረዘሩትን ለመፈጸም የሚቻለንን ሁሉ ለማድረግ ያለንን ዝግጁነት እየገለጽን፣ መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ወያኔና ግብር አበሮቹ ከፊቱ የደቀኑበትን ከፍተኛ አደጋ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ተባብሮ እንዲያስወግድ ግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ ጥሪውን ያቀርባል።

አስቸጋሪ ወቅት ላይ የምንገኝ ቢሆንም እንኳን በርትተን ከታገልን የተረጋጋች፣ ዲሞክራሲያዊ ሉዓላዊ አገር - ኢትዮጵያ - ይኖረናል። ለዚህ ውጤት በርትተን እንታገል።

**ክብር የግንቦት 7 1997 ሀገራዊ ተስፋን እውን ለማድረግ ለወደቁ ሰማዕታት !**

**ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ !!!**

**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**

**መካከኛ ሞገድ፡-** በ 358 MB, በ 837 kHz

**አጭር ሞገድ፡-** በ 31 MB በ 9700 KHz

በ 41 MB በ 7185, በ 7175 በ 7160 እና በ 7120 KHz

በ 49 MB በ 5980 KHz እና በ 60 MB 4760 GHz

ላይ ዘወትር ማክሰኞ እና ሐሙስ ከጠዋቱ 2:30 እስከ 3:00 ሰዓት በድጋሚም ከሰዓት በኋላ 11:30 እስከ 12:00 ሰዓት እንዲሁም ዘወትር ቅዳሜ ከጠዋቱ 3:00 እስከ 3:30 ሰዓት እንዲሁም ከሰዓት በኋላ ከምሽቱ 11:30 እስከ 12:00 ሰዓት የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ በስልክ ወይም በኢሜል በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታሳውቁን እንገልጻለን።

ማሳሰቢያ፡- ሰዓቱ በኢትዮጵያ የሰዓት አቆጣጠር ነው።

**ውድ አንባቢዎቻችን**

ለፕሮግራማችን ይበጀል ያስተምራል ብላችሁ የምታሳስቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዮን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org

## ዜጎችን ደም የሚያፋስስ የዘር ፍጅት ሊነሳ እንደሚችል የጊምቢ ነዋሪዎች አስጠነቀቁ

በኦሮምያ ክልል በምእራብ ወለጋ በጊምቢ ከተማ ነዋሪ የሆኑ የአማራ ተወላጆች፣ ከአካባቢው እንዲወጡ በሚፈልጉ ወጣቶች ቤታቸው እየተደበደበ መሆኑንና ህይወታቸውም አደጋ ላይ መውደቁን ተናግረዋል። አንድ ከወሎ አካባቢ የመጡ የመንግስት ሰራተኛ የኦሮሞ ተወላጅ የሆኑ ባለቤታቸውን አግብተው ለዘመናት ከኖሩ በሁዋላ፣ ሰሞኑን ወደ መጣህበት ሂድ ተብለው በባለቤታቸው ልመና ከሞት እንደተረፉና የቤታቸው ጣሪያም ወንፊት እንደሆነባቸው እያለቀሱ ተናግረዋል።

ባለቤታቸውም በከተማዋ ውስጥ ያንዣበበውን አደጋ በተመለከተ በኦሮምኛ ቋንቋ ስሜታቸውን ገልጸዋል። ህወሃት ከኦህዴድ ጋር በመሆን የአማራንና የኦሮሞን ብሄሮች ለማጋጨት እቅድ መንደፋን እና ህዝቡ አስፈላጊውን ጥንቃቄ እንዲያደርግ ኢሳት ሲያሳስብ ቆይቷል። ህወሃትና ኦህዴድ ያሰማሩዋቸው ካድሬዎች ”ኦሮሞው” ባህርዳር ላይ ተሰደበ በሚል ከአዲስ አበባ የመሬት መስፋፋት ጋር በተያያዘ የተነሳውን ጥያቄ የብሄር አጀንዳ ለመስጠት እየሞከሩ ነው። በጄ/ል ከማል ገልቹ የሚመራው ኦነግ፣ በአቶ ሌንጮ ለታ የሚመራው የኦሮሞ ዲሞክራሲ ንቅናቄ፣ በአገር ውስጥ የሚንቀሳቀሱት የኦሮሞ ፌደራሊስት ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ የኦሮሞ ወጣቶች ትኩረታቸውን በህወሃት አገዛዝ ላይ ብቻ እንዲያደርጉ ማሳሰባቸው ይታወቃል።